# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አንድ (1ኛ ዮሐ 1፡1-10)

1. ‹‹እናውጃለን›› የሚለው ቃል በቁ1፣ 2፣ እና 3 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ሁለቱም በመጀመሪያ በነበረው ነገር ላይ ያተኮሩ ሲሆን የሚናገሩትም ቃል ስለሆነው ስለኢየሱስ ነው፡፡
2. እናውጃለን የሚሉት በመጀመሪያ የነበረውን፣ የሰሙትን፣ ያዩትን፣ የተመለከቱትንና በእጃቸው የዳሰሱትን ነው፡፡ ይህ የታየውና የተሰማው የህይወት ቃል ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ ይህ ሰማን፣ አየን፣ ተመለከትንና ዳሰስን የሚለው አነጋገር የነገሩን እርግጠኛነትና እውነተኛነቱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡
3. ይህ ህይወት የዘላለም ህይወት ነው፣ በአብ ዘንድ የነበረ ነው፣ ለሐዋርያቱ ተገልጧል፡፡
4. የመጀመሪያው ምክንያት ከእነርሱ ጋራ ህብረት እንዲኖራቸው (ይህም ህብረት ከአብና ከወልድ ጋራ እንደሆነ) ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ የእነ ዮሐንስ ደስታ ሙሉ እንዲሆን ነው፡፡
5. ይህ ክፍል የሚናገረውን እውነት በአንድ ዓረፍተ ነገር ለመጠቅለል ቢያስፈልግ፣ ‹‹እግዚአብሄር ብርሃን ነው በእርሱም ዘንድ ጨለማ የለም›› የሚለው ይሆናል፡፡
6. ‹‹ብንል›› የሚለው ቃል ሶስት ጊዜ በቁ5-10 ውስጥ ሶስት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን በቁ6 ላይ ያለው ከእርሱ ጋራ ህብረት አለኝ እያለ በጨለማ ስለሚመላለስ ሰው፣ ቁ8 ላይ ደግሞ ያለሐጥያት ነኝ የሚል ራሱን እንደሚያስትና በቁ10 ደግሞ ሃጥያት አላደረኩም የሚል እግዚአብሄርን ውሸተኛ እንደሚያደርግ ነው፡፡
7. እነርሱ መልዕክቱን ከእርሱ ከራሱ እንደሰሙት፣ መልዕክቱን ለእነርሱ እንዲያስተላልፉ የተሰጣቸው እነደሆነ፣ እግዚአብሄር ብርሃን እንደሆነና በእርሱ ዘንድ ጨለማ እንደሌለ፡፡
8. ደስታ የሚገኘው የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ በመፈጸም ስለሆነና ወንጌልን ላልሰሙት ማሰማት ደግሞ ፈቃዱን መፈጸም ስለሆነ በአማኝ ልብ ውስጥ ትልቅ የደስታ ምንጭ ይሆናል፡፡ የተቀረውን ጥያቄ እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይግለጥ፡፡

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሁለት (1ኛ ዮሐ 2፡1-6)

1. መልዕክቱን የጻፈላቸው ልጆቼ የሚላቸው አማኞች ነው፡፡ የጻፈበት ምክንያትም ሃጥያት መለማመድ እንደሌለባቸው ለመንገርና ሃጥያት ቢያደርጉ ግን ጠበቃ እንዳላቸው ለመንገር፡፡
2. አንደኛው አማኝ በሐጥያት መመላለስ እንደማይኖርበትና ሁለተኛው ደግሞ ተሸንፎ ወይም ተሳስቶ ሃጥያት ላደረገ ደግሞ ክርስቶስ በሰማይ ጠበቃ እንዳለው የሚሉት ናቸው፡፡
3. ከአባቱ ጋራ ስለ እኛ ይነጋገራል፣ ጻድቅ ነው፣ የሐጥያት መስዋዕት ሆኗል፣ ለመላው ዓለም ሐጥያት መስዋዕት ሆኗል፡፡
4. እኛ እያለ የሚናገረው አማኞችን ሲሆን እርሱ የሚለው ደግሞ ኢየሱስን ነው፡፡ ኢየሱስን አውቄዋለሁ ለማለት ማረጋገጫ ሆኖ የቀረበው ትዕዛዙን መጠበቅ ነው፡፡
5. አውቄዋለሁ የሚል ትዕዛዙን ግን የማይጠብቅ ሰው ነው ውሸተኛ በመባል የተነገረለት፡፡ በተጨማሪ ስለዚህ ሰው የሚናገረው፣ እውነት በእርሱ ውስጥ እንደሌለ ነው፡፡
6. አማኝ የእግዚአብሄርን ቃል ሰምቶ በህይወቱ ወደ መታዘዝ ሲያደርሰው የእግዚአብሄር ፍቅር በእርሱ ውስጥ ፍጹም ይሆናል፡፡
7. በዚህ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ እንደተራመደው/እንደተመላለሰ መመላለስ በእርሱ ውስጥ ለመሆናችን በማረጋገጫነት ተጠቅሷል፡፡
8. እያንዳንዱ የራሱን ምላሽ ይስጥበት፡፡

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሶስት (1ኛ ዮሐ 2፡7-17)

1. ከዚህ ቁጥር አንባቢዎቹ ወዳጆቹ/አማኞች ሊሆኑ እንደሚችሉ እናያለን፡፡ መልዕክቱ ደግሞ አዲስ ትዕዛዝ እንዳልሆነና ቀድሞ የሚያውቁት ነገር መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡
2. ተቃራኒ የሚያስመስላቸው፡ ቁ7 ትእዛዙ አዲስ አይደለም ሲል ቁ8 ደግሞ አዲስ ማለቱ ነው፡፡ የአሁኑን ትዕዛዝ አዲስ የሚያደርገው ራስን ለሌሎች እስከመስጠት የሚያደርገውን የክርስቶስ ፍቅር በቀድሞው ትዕዛዝ ይህ አለመኖሩ ነው፡፡
3. በዚህ ክፍል የሚያነጻጽረው ወንድሙን የማይወደውንና ወንድሙን የሚወደውን ሰው ነው፡፡
4. ወንድሙን የሚጠላ ሰው፡ በጨለማ ውስጥ እንዳለ፣ በጨለማ እንደሚመላለስ፣ ጨለማ እንዳሳወረውና የሚሄድበትንም እንደማያውቅ ሲነገረን፣ ወንድሙን የሚወድ ደግሞ፡ በብርሃን እንደሚኖርና መሰናከያ እንደሌለበት ይነግረናል፡፡
5. የጻፈው፡ ልጆች ሃጥያታቸው በስሙ ስለተሰረየላቸው፣ አባቶች አብን ስላወቁና ጎበዛዝቱ ደግሞ ክፉውን ስላሸነፉ ነው፡፡ በተለይ የጎበዛዝቱ ክፉውን ማሸነፍ የተያያዘው የእግዚአብሄርን ቃል በውስጣቸው ስለሰወሩ ነው፡፡ መዝ 119፡11
6. ተደጋግሞ በቁ15-17 ውስጥ የሚገኘው ‹‹ዓለም›› የሚለው ቃል ነው፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ያለው በአንድ ዓረፍተ ነገር ሲጠቀለል፡ አባትን ወይም ዓለምን መምረጥ ግድ ነው፣ በተከፋፈለ ልብ አማኝ መመላለስ አይችልምና የመሳሰሉ ዓረፍተ ነገሮችን መገንባት ይቻላል፡፡
7. እነዚህ ሶስት ሃሳቦች በቁ16 ላይ የተዘረዘሩት፤ የሥጋ ምኞት፣ የዓይን አምሮትና የኑሮ ትምክህት የሚሉት ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ዓለም ሲል በ1ኛ ዮሐ 5፡19 አስተሳሰብን፣ ነገሮችን የምናይበት ሚዛን መለኪያና መስፈርታ እንዲሁም አመለካከትን ሁሉ ይጠቀልላል፡፡
8. አማኝ መጠየቅ ያለበት አንድ ጥያቄ፡ ‹‹ወንድሜንና እህቴን እወዳለሁ ወይስ አልወድም?›› የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡ እያንዳንዱ ለራሱ ይመልስ፡፡

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አራት (1ኛ ዮሐ 2፡18-29)

1. የክርስቶስ ተቃዋሚ በማለት በነጠላ የሚጠራው በመጨረሻ ሊገለጥ ያለውን ሃሰተኛውን ክርስቶስ የሚያመለክት ሲሆን፤ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች እያለ በብዙ ቁጥር የሚናገረው ደግሞ በማንኛውም ዘመን ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉትን ክርስቶስ አይደለም በማለት ኢየሱስን የሚክዱትን ሰዎች ነው፡፡
2. ‹‹እኛ›› የሚለው በክርስቶስ ያመኑትን እውነተኛ አማኞች ሲሆን ወጡ፣ አልነበሩም እና ተለዩ የሚላቸው ደግሞ በእውነተኛ አማኞች መሃል ሳያስታውቁ የቆዩና ቆይቶ ግን ማንነታቸው የተገለጠባቸው ሰዎችን ነው፡፡ ይህ ክፍል የሚናገረው ከአጥቢያ ቤ/ክ ስለመውጣት ሳይሆን በቁ18 ላይ ስለተነገረው ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን በመካድ ከቅዱሳን መለየት ነው፡፡
3. የሚያነጻጽራቸው ሁለት አይነት ሰዎች፡ ከቅዱሳን መሃል የወጡትን ካልወጡት ጋራ ነው፡፡ እነዚህን ሁለት አይነት ሰዎች የሚለዩአቸው ሁለት ነገሮች፡ አንደኛው ከእርሱ ቅባት የተቀበሉ ሰዎች ሲሆኑ፣ ሌላው ደግሞ ሁሉም እውነትን ያውቃሉ፡፡
4. እውነትን ለማያውቁ ሰዎች መጻፍ ማለት ቅባቱ/መንፈስ ቅዱስ ለሌላቸው ሰዎች መጻፍ ስለሚሆን የእግዚአብሄርን እውነት ለእንደዚያ አይነት ሰዎች ቢጽፍ ሞኝነት ሲሆን ሊረዱት አይችሉም፤ እነዚህ ግን ቅባቱ ስላላቸው የሚጽፍላቸውን እውነት ለመረዳት ችሎታ አላቸው ማለቱ ነው፡፡
5. አንድ ሰው ክርስቶስ አይደለም ብሎ ስለኢየሱስ ከተናገረ ሐሰተኛ ለማለት እንችላለን፡፡ ወልድን ካደ ማለት አብን ካደ ማለት ነው፣ ወልድን የካደ አብ አለኝ ሊል አይችልም፣ ወልድን ያመነ አብ አለው፤ ማለትም ወልድን አመነ ሲበል ከአብ እንደተላከ፣ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑና ሁሉን ያጠቃልላል፡፡
6. ቅባቱ ከእርሱ የተቀበልነው ነው፣ ቅባቱ በውስጣችን ነዋሪ እንጂ ጊዜያዊ አይደለም፣ ቅባቱ ያለው ሌላ አስተማሪ አያስፈልገውም፣ ቅባቱ ሁልጊዜ እውነት ነው፣ ቅባቱ የሚያስተምረን ስለሁሉም ነገር ነው፡፡ ይህ ክፍል ተደጋግሞ የተነገረን ቅባቱ እውነትን የሚያስተምረን እንደሆነ ነው፡፡ ማንኛውም የወንጌል አስተማሪ ሲያስተምር አውነቱንና ሐሰቱን መለየት የሚችለው ዋነኛው አስተማሪ በውስጣችን መኖሩ ነገሮችን አግበስብሰን ውስጣችን እንዳናስገባ ቅባቱ ያስተምረናል ማለት ነው፡፡
7. እንዳስተማረን እንድንኖር ሲናገር ምርኩዝ ያደረገው ነገር ከላይ ቅባቱ ሁሉንም እንዲያስተምረንና ደግሞም እርሱ የሚያስተምረን ነገር እውነት እንጂ ውሸት እንደማይቀላቀል ስለምናውቅ ነው፡፡ በቁ28 ላይ ተጨማሪ የምናያቸው ማበረታቻዎች፡ አንዱ እርሱ ሲገለጥ ድፍረት እንዲኖረንና፣ ሌላው ደግሞ በሚመጣበት ጊዜ በፊቱ እንዳናፍር የሚሉት ናቸው፡፡
8. አንድ ወንድሜ/እህቴ ቅባቱን እንድትቀበል ልጸልይልህ ቢለኝ ስላሰበልኝ አመስግኜ ነገርግን ለዚህ ጸሎት እንደማልፈልግ እነግራለሁ፤ ምክንያቱም ለእግዚአብሄር ካህን እንድሆን ያበቃኝ ያ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በእኔ ውስጥ ስላለ ማለት ነው፡፡

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አምስት (1ኛ ዮሐ 3፡1-10)

1. በዚህ ክፍል የእግዚአብሄር የፍቅር ማረጋገጫ ሆኖ የቀረበው የእግዚአብሄር ልጆች መባላችን ነው፡፡ አለም እኛን አያውቀንም ሲል፤ አባታችንን ስላላወቀ እኛ ያገኘነውን ደስታ፣ ሰላም፣ በረከትና መልካም ነገር ሁሉ ሊረዳ አይችልም፤ እንዲያውም በአለም ያለውን ደስታ ሁሉ ያጣን ምስኪኖች ሆነን ነው ለአለም የምንታየው ማለት ነው፡፡
2. ወደፊት ምን እንደምንሆን አናውቅም ነው የሚለው፡፡ ስለወደፊቱ ዛሬ የምናውቃቸው ሁለት ነገሮች፤ የመጀመሪያው እርሱ ሲገለጥ እንደምናየውና ሌላው ደግሞ እርሱን እንደምንመስል ማወቃችን ናቸው፡፡
3. ይህ ተስፋ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ሲሆን ይህም ተስፋ በንጽህናና በቅድስና እንድንመላለስ ነው የሚያበረታታን፡፡
4. እርሱ እያለ የሚናገረው ኢየሱስን ነው፡፡ ስለኢየሱስም የተነገሩት ሁለት እውነቶች፡ ሃጥያትን ሊያስወግድ መገለጡና በእርሱም ሃጥያትን እንደሌለ ናቸው፡፡
5. በእርሱ የሚኖር ሃጥያት አያደርግም፣ ሃጥያት የሚያደርግ ደግሞ አላወቀውም፣ አላየውም፡፡ ሐጥያት አያደርግም ማለት ከሃጥያት ነጻ ነው ማለት እንዳልሆነ ከ1ኛ ዮሐ1፡8-9 እንረዳለን፤ ስለዚህ ይህ ማለት ሃጥያትን ያለንስሃና ህሊናውን ሳይቆረቁረው በደስታ ተዝናንቶ የሚያደርግ ከሆነ እግዚአብሄርን አውቃለሁ ማለት አይችልም፡፡የእንግሊዝኛው መ/ቅ ይህንን አመለካከት ነው በትክክል ያሰፈረው፡፡
6. ምክንያቱም ከእግዚአብሄር የተወለደ ሰው የእርሱ ዘር በውስጡ ስላለ ሃጥያትን የመጸየፍና የመጥላት ነገር ውስጡ መኖሩ ግድ ነው፡፡
7. ሁለቱን የሚለዩአቸው ነገሮች፡ የመጀመሪያው የእግዚአብሄር ልጆች ጽድቅን የሚያደርጉ ሲሆን የዲያቢሎስ ልጆች ደግሞ ሃጥያትን የሚያደርጉ ናቸው፤ ሌላው ደግሞ የእግዚአብሄር ልጆች ወንድሞቻቸውን የሚወዱ ሲሆን የዲያቢሎስ ልጆች ግን ወንድሞቻቸውን የሚጠሉ ናቸው፡፡
8. የጌታን መገለጥ ስንጠባበቅ ህይወታችንን በንጽኅና ለመጠበቅም አስፈላጊውን ነገሮች ማድረግ ይኖርብናል፡፡ እያንዳንዱ ሃሳቡን ይናገር፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ስድስት (1ኛ ዮሐ 3፡11-24)

1. ከመጀመሪያው የሰሙት ትዕዛዝ እርስ በእርሳችን እንዋደድ የሚለው ሲሆን ይህንን ህግ በመጀመሪያ የተላለፈው ሰው ቃየን ነው፤ ይህንንም ያረጋገጠው ወንድሙን በመግደል ነበረ፡፡
2. ጸሐፊው ይህንን ቃየን በአቤል የጽድቅ ሥራ ከፋቱ ሲጋለጥ ጠልቶ እንደገደለው፤ እኛም የክርስቶስ ዓይነት ኑሮን ከኖርን ጽድቃችን የዓለምን ሥራ ስለሚያጋልጥ ይጠላናል ማለቱ ነው፡፡ ከሞት ወደ ህይወት የመሸጋገር አንዱ መለኪያ ሆኖ በዚህ ክፍል የቀረበው፣ ወንድምን መውደድ መሆኑን ከቁ14 መረዳት እንችላለን፡፡
3. ክርስቶስ ስለእኛ ራሱን አሳለፎ መስጠቱን ነገር ስናይ የእውነተኛ ፍቅርን ምንነት እናያለን፡፡ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገልንን ከተረዳንና ካወቅን እኛ ደግሞ የእርሱን ፈለግ በመከተል ህይወታችንን ለወንድሞቻችን የመስጠት ሃላፊነት አለብን ማለት ነው፡፡
4. በቁ17 መሰረት ለተቸገረ ወንድም/እህት ራርቶ ጎዶሎን መሙላት ነው ራስን ለሌላ መስጠት፡፡ ሃብት ያለው ብሎ ደግሞ የሚናገረው የለውን የገንዘብ መጠን ሳይሆን ሊያደርግ የሚችለው ማናቸውንም ያህል ለማድረግ የሚደረግን የልብ ፈቃደኛነት እንደሚያመለክት ቁ18 ይጠቁማል፡፡
5. ብዙ ጊዜ ማድረግ እየቻልን እጸልይልሃለሁ ወይም ስለችግርህ ጉዳይ ወንድም እገሌን አነጋግረሃል? ቤተክርስትያን ምን አለችህና የመሳሰሉትን የከንፈር ቋንቋዎች በመጠቀም ሃላፊነቱን ከራሳችን ስንገፋ እንገኛለን፤ ይህንን ነው ጸሐፊው የሚናገረው፡፡ ‹‹ብቻ›› የሚለው ቃል የሚጠቁመን፤ ቢቃልና በአንደበት ብቻ ፍቅርን መግለጽ ልክ እንዳልሆነ ነገርግን ከተግባር ጋራ ከሆነ በአንደበትም ፍቅርን መግለጽ መልካም እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡
6. አንደኛ ይህንን በማድረጋችን ከእውነት ወገን ለመሆናችን ማረጋገጫ ይሰጠናል፣ ሌላው ደግሞ ልባችን በእኛ ላይ በሚፈርድብን ነገርም ልባችንን በፊቱ እናሳርፋለን፤ ማለትም ማድረግ የሚገባንን እንዳላደረግና ግብዞች ከሚል የህሊና ወቀሳ ውስጥ እንወጣለን ማለት ነው፡፡
7. ሁለቱ ቅድመ ሁኔታዎች፡ ትዕዛዙን መጠበቅና ደስ የሚያሰኘውን ማድረግ ናቸው፡፡ ትዕዛዞቹም በቁ23 ላይ የሰፈሩት፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንና እርስ በእርስ መዋደድ ናቸው፡፡
8. ኢየሱስ ክርስቶስ እወዳቸዋለሁ ብሎ ብቻ አይደለም ለአብ የነገረው፤ ነገር ግን ስለእኛ ራሱን ለመስጠትና ለሞት እንዲያውም ለመስቀል ሞት ራሱን አሳልፎ ስለሰጠ እርሱ ምሳሌአችን ነው፡፡

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሰባት (1ኛ ዮሐ 4፡1-6)

1. እንዳያደርጉ የሚያዛቸው መንፈስን ሁሉ እንዳያምኑ ሲሆን እንዲያደርጉ የሚጠይቃቸው ነገር ደግሞ መናፍስት ከእግዚአብሄር መሆናቸውን እንዲመረምሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙ ሐሰተኞች መናፍስት ወደ ዓለም ወጥተዋልና ነው፡፡
2. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እውነተኛውን ከሐሰተኛው ለመለየት የተሰጣቸው ሃሳብ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ መምጣቱን ካላመነ ከሀሰተኛው እንደሆነ ነው የነገራቸው፡፡ የኢየሱስን በስጋ መምጣት የማይቀበል የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ እንደሆነ ነው የሚያረጋግጥላቸው፡፡
3. ‹‹አሁንም በዓለም አለ›› የሚለው የክርስቶስ ተቃዋሚን መንፈስ ነው፡፡ ሐሰተኛው ክርስቶስ በመጨረሻ ዘመን የሚገለጥ እንደሆነ 2ኛ ተሰ 2፡1-12 የሚነግረን ሲሆን ይህ ክፍል ግን የሚናገረው መንፈሱ በሁሉም ዘመን ውስጥ የሚሰራ እንደሆነና የእርሱን ነገር በሚያንጸባርቁት ውስጥ ራሱን እንደሚገልጥ የታወቀ ነው፡፡
4. እናንተ ሲል እውነተኞቹን አማኞች ሲሆን እነርሱ ሲል ግን ሐሰተኞቹን ማለቱ ነው፡፡ አማኞች፡ ከእግዚአብሄር ናቸው፣ እነርሱን አሸንፈዋል፣ እግዚአብሄርን የሚያውቅ ይሰማቸዋል፣ ከእግዚአብሄር ያልሆነ አይሰማቸውም፤ ሐሰተኞቹ፡ ከዓለም ናቸው፣ እንደ ዓለም ይናገራሉ፣ ዓለም ይሰማቸዋል፡፡
5. እናንተ የተባት እውነተኞቹ አማኞች ሐሰተኞቹን ያሸነፉበት ምክንያት በእነርሱ ውስጥ ያለው በዓለም ወይም በሐሰተኞቹ ውስጥ ካለው በመብለጡ ነው፡፡ በአማኞቹ ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ሲሆን በሐሰተኞቹ ውስጥ ደግሞ ያለው የሐሰተኛው መንፈስ ነው፡፡
6. እናንተ የተባሉት ከእግዚአብሄር መሆናቸው በኑሮ፣ በንግግርና በድል ነሺነት መሆራቸው ከእውነት ለመሆናቸው ህይወታቸው ማረጋገጫ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እነርሱ የተባሉት ኑሯቸው፣ ንግግራቸውና ተሸናፊነታቸው ግልጽ ሆኖ መታየቱ ከሌላ ወገን መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡
7. 1-3 ያሉት ቁጥሮች እውነተኛንና ሐሰተኛን መንፈስ በትምህርቱ ዓይነት መለየት እንደሚቻልና 4-6 ደግሞ ሰዎችን በአኗኗራቸው ከየትኛው ካምፕ እንደሆኑ መለየት እንደሚቻል ያስረዳናል፡፡
8. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይግለጽ

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ስምንት (1ኛ ዮሐ 4፡7-21)

1. ፍቅር ከእግዚአብሄር ነው፣ የሚወድ ከእግዚአብሄር ተወልዷልና የሚወድ እግዚአብሄርን ያውቃል የሚሉት ናቸው፡፡
2. ምክንያቱም እግዚአብሄር ፍቅር ስለሆነና እግዚአብሄርን ማወቅ ፍቅርን ማወቅ ስለሆነ የማይወድ ፍቅርን ወይም እግዚአብሄርን አውቀዋለሁ ለማለት አይችልም፡፡
3. የኢየሱስን መምጣት በቀጥታ ከእግዚአብሄር ፍቅር ጋራ ነው የሚያያይዘው፡፡ በህይወት እንኖር ዘንድ ያደርገናል፣ ሐጥያታችንን ያስተሰርይልናል፡፡
4. ጸሐፊው ከ7-10 ያሉትን ያሰፈረበት ምክንያት የእግዚአብሄርን ምሳሌነት በመከተል እርስ በእርሳችን እንድንዋደድ ሲሆን ከዚያም በተጨማሪ ‹‹እንዲህ ከወደደን›› የሚለው አነጋገር መጠኑንም ጭምር እንድንገነዘብ የሚፈልግ ይመስላል፡፡
5. ቁ13 ለአማኞች የሚያረጋግጥልን ሃሳቦች፡ ሁላችን መንፈሱን እንደተቀበልን፣ እኛ በእግዚአብሄር ውስጥ እንዳለንና እግዚአብሄር ደግሞ በእኛ ውስጥ እንዳለ እንረዳለን፡፡ አብ ልጁንና መንፈሱን ሰጠን፣ ወልድ ደህንነት ሰጠን፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በእርሱ ለመኖራችንና እርሱም በእኛ ለመኖሩ በውስጣችን እርግጠኞች እንድንሆን አደረገን፡፡
6. አብ ኢየሱስን እንደላከ አይተናል፤ ደግሞም ይህንን ያየነውን እንመሰክራለን ይላል፡፡
7. ይህ በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልናል የሚለው አንድ ነገር ‹‹ፍቅር›› ነው፡፡
8. በቅድሚያ የወደደን እርሱ መሆኑንና አሁን እኛም እንደምንወደው፣ እግዚአብሄርን እወዳለሁ እያሉ ወንድምን መጥላት ውሸታምነት እንደሆነ፣ ያየነውን ወንድማችንን ካልወደድን እግዚአብሄርን መውደድ እንደማንችል፣ እግዚአብሄርን ከወደድን ወንድማችንንም የመውደድ ትዕዛዝ እንዳን፡፡
9. እርሱን መምሰላችን ሊገለጥ የሚችልበት ዋነኛው መንገድ በፍቅር ስለሆነ ያ ፍቅር በወንድሞችና በእህቶቻችን ላይ ተገልጦ ሊታይ ያስፈልጋል፡፡

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ዘጠኝ (1ኛ ዮሐ 5፡1-21)

1. ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ማመን ነው ምልክቱ፡፡ በቁ1 ‹‹ልጁን›› የሙለው ከቀደመው ሃሳብ ጋራ ተያይዞ ኢየሱስን(አንድ ልጁን) የሚጠቁም ሲሆን በቁ2 ላይ ግን ‹‹ልጆቹ›› የሚለው እኛን ሁሉ የሚጠቀልል ሃሳብ ነው፡፡
2. እግዚአብሄርን ስንወድና ትዕዛዛቱን ማለትም(ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚለውን) ስንጠብቅ የእርሱን ልጆች መውደዳችን ማረጋገጫ ይሆናል፡፡
3. ምክንያቱም እኛ ከእግዚአብሔር ስለተወለድንና ከእርሱ የተወለደ ደግሞ ዓለምን ስለሚያሸንፍ ነው፡፡ አለም የሚሸነፈው በእምነት ነው፡፡ በዚህ ክፈል አነጋገር እምነት ማለት ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ የምናምነው እምነት ነው፡፡ ቁ5 ተመልከት፡፡
4. በዚህ ክፍል ምስክርነት የሚለው ሃሳብ 8ጊዜ ተጠቁሷል፡፡ አዎ፣ የእግዚአብሄር ምስክር ከሰው ምስክር እንደሚበልጥ ቁ9 ያረጋግጥልናል፡፡ እግዚአብሄር ስለልጁ በብዙ ሥፍራ የመሰከረ ሲሆን ማቴ 3፡17 ከእነዚህ አንዱ ነው፡፡
5. መልዕክቱ የተጻፈው በእግዚአብሄር ልጅ ስም ለሚያምኑ ሲሆን፤ የተጻፈበትም ምክንያት የዘለዓለም ህይወት እንዳላቸው ሙሉ እርግጠኛ እንዲሆኑ ነው፡፡
6. ከእግዚአብሄር የተወለደ ሁሉ፡ 1ኛ) ሃጥያት እንደማያደርግ 2ኛ) የእግዚአብሄር ልጅ እንደሚጠብቀውና 3ኛ) ክፉው እንደማይነካው እናውቃለን፡፡ ሃጥያት እንደማያደርግ የሚለው ቃል ፍጹምነትን የሚያመለክት ሳይሆን በፈቃደኛነት ሁልጊዜ በሃጥያት አይመላለስም ማለቱ ነው፡፡
7. እኛ ከእግዚአብሄር እንደሆንን፣ መላው ዓለም በክፉው ሥር እንደሆነ፣ የእግዚአብሄር ልጅ እንደመጣና እርሱን እንድናውቅ ማስተዋልን እንደሰጠን እናውቃለን፡፡
8. በ2ኛ ጢሞ 2፡22 ሥጋን የምናሸንፈው በመሸሽ፣ ያዕ 4፡7 ሰይጣንን በመጋፈጥና ጸንቶ በመቆም የምንዋጋ ሲሆን 1ኛ ዮሐ 5፡4-5 ደግሞ ዓለምን የምናሸንፈው በእምነት እንደሆነ ሰፍሮልናል፡፡ ከየትኛው ጠላት ጋራ እንደምንገጥም ማወቃችን የሚጠቅመን የትኛውን ዘዴ መጠቀም እንደሚኖርብን ለመወሰን ይረዳናል፡፡